የተወደዳችሁ የመላው አውሮፓ ጉባኤ ተሳታፊዎች

ይህች አጭር የጉዞ መመሪያ የተዘጋጀው እናንተን ከተለያዩ ሀገራት ወደ ጉባኤው ቦታ የምታደርጉትን ጉዞ ይረዳል ብለን በማሰብ ነው።

## የአውሮፕላን ቲኬት

ቲኬት እስካሁን ላልገዛችሁ እንደ ዋጋውና ምቾቱ ርቀት መጠን ከሚከተሉት ድህረ ገጾች ማግኘት ይቻላል።

www.cheapflights.co.uk , www.ryanair.com , www.easyjet.com ,

www.expedia.com, www.bmi.com, www.opodo.com , ወዘተ

## የለንደን አውሮፕላን ማረፊያዎች

ከአብዛኛው የአውሮፓ ሀገሮች ወደ ለንደን መምጣት የሚቻልባቸው አውሮፕላን ማረፊያዎች የሚከተሉት ናቸው። ሂትሮው (Heathrow Airport), ጋትዊክ ( Gatwick Airport), ስታንስተድ (Stansted Airport), ሉተን (Luton Airport)

## እንግዶች መቀበያ ጣቢያ

ባለፈው በላክንላችሁ አጭር የጉባኤ መረጃ ሁሉንም የአውሮፓ ሀገራት ተሳታፊዎች የምንቀበለው ከቤተ ክርስያናችን አቅራቢያ ካለው ሆሎዌይ ሮድ ( Holloway Road Station ) የባቡር ጣቢያ መሆኑን ልብ ይሏል።

## ጉዞ ከተለያዩ የአውሮፕላን ማረፊያዎች

### ከሂትሮው አየር ማረፊያ ( Heathrow Airport )

በዚህ አየር ማረፊያ ለሚመጡ ተሳታፊዎች ብቻ ወደ ጉባኤው ቦታ የሚያደርጉት ጉዞ ከሌሎቹ አንጻር በጣም ቀላል ይሆንላቸዋል። ይኸውም ከአየር ማረፊያው ከላይ ወደ ተገለጸው የመቀበያ ባቡር ጣበያ በአንድ ጉዞ የሚደረስ በመሆኑ ነው።

ስለዚህ ከባቡር ጣቢያው የቲኬት ማሽን ወይም ሱቅ ወደ ሆሎዌይ ባቡር ጣበያ የሚያደርስ ቲኬት (single ticket to Holloway Station) በመግዛት ቀጥታ ሆሎዌይ ባቡር ጣቢያ ያለምንም ችግር ከሚመደቡት እንግዳ ተቀባዮች ጋር በመገናኘት ተመስገን እዚህ ያደረስከኝ ማለት ብቻ ይጠበቅብና ል።

### ከጋትዊክ፣ከስታንስተድ፣ከሉተን አየር ማረፊያ ( Gatwick, Stansted and Luton Airport )

እነዚህ የአየር ማረፊያዎች በመጠኑ ከለንደን ወጣ ያሉ በመሆናቸው ወደ መሐል ለንደን ለመምጣት እያንዳንዱ ተሳታፊ የክፍለ ሀገር አውቶብስ ( Coach ) ወይም ባቡር መሳፈር ይጠበቅበታል።

የባቡሩን ወይም የአውቶብሱን ቲኬት ከዚያው ከአየር ማረፊያው ገዝቶ ተሳፍሮ መምጣት ይቻላል። ሁሉም ባቡሮች ቪክቶሪያ (Victoria Train Station ) ወይም ሊቨርፑል መንገድ (Liver pool Street station) ባቡር ጣቢያዎች ሲያደርሱን ሁሉም አውቶብሶች ቪክቶሪያ አውቶብስ ጣቢያ  (Victoria Coach Station) ያደርሱናል።

Fig.1. ለንደን ቪክቶሪያ ባቡር ጣቢያ እና አውቶብሰ ጣቢያ ( Victoria Underground Train and Coach Station )




Victoria Coach Station

ቪክቶሪያ አውቶብስ ጣቢያ

Victoria Train Station

ቪክቶሪያ ባቡር ጣቢያ

ሊቨርፑል መንገድ ባቡር ጣቢያ

Liver pool street Train station




Fig.2. ሊቨርፑል መንገድ ባቡር ጣቢያ (Liverpool Underground Train Station )

እነዚህ ባቡሮች ሉተን ፣ጋትዊክ እና ስታንስተድ ኤክፐረስ (Luton Express, Gatwick Express and Stansted Express) በመባል ሲጠሩ አውቶብሶቹ ደግሞ ናሽናል ኢክስፐረስ (National Express ) በመባል ይጠራሉ።

ስለዚህ ከዚህ በታች የሚሆነው ገለጻ እነዚህ ባቡሮች ወይም አውቶብሶች ከሚያደርሱበት ጣቢያ ማለትም ከቪክቶሪያ, ከሊቨርፑል መንገድ እና ከሂትሮው ጀምሮ ይሆናል ማለት ነው።

በስዕሉ ላይ እንደሚታየው የምድር ውስጥ ባቡር (Underground Train) ካርታ ላይ ተሳታፊው ከአየር ማረፊያው ተነስቶ የሚደርስበት ባቡር ጣቢያና ሆሎዌይ ባቡር ጣቢያ ተመልክተዋል።

Fig.3.የምድር ውስጥ ባቡርን መስመሮች የሚያሳይ ካርታ (Underground train lines/ Tube Map)




ሂትሮው ባቡር ጣቢያ / አየር ማረፊያ ቪክቶሪያ ባቡር ጣቢያ ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ ሊቨርፑል መንገድ ባቡር ጣቢያ

**Heathrow airport/ Train Station Victoria Train Station Holloway Road Train Station Liver pool Street Station**

ይህን የባቡር መስመር በሚገባ ለመጠቀም በ http://www.tfl.gov.uk/assets/downloads/standard-tube-map.gif ድህረ ገጽ ያገኙታል። ከላይ በስዕሉ እንደምናየው የምድር ውስጥ የባቡር ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚያሳዩ የጉዞ መስመሮች ከአስር የሚበልጡና የተለያየ ቀለማት ያላቸው ናቸው። ለዚህ ጉዞአችን የምንጠቀምባቸው የመስመር ቀለማት ቢየንስ አምስቱን ይሆናል።

እነዚህም

1. PICADILLY LINE
2. VICTORIA LINE
3. CIRCLE LINE
4. METROPOLITAN LINE
5. HAMMERSMITH AND CITY LINE በመባል ይታወቃሉ።

ማሳሰቢያ፡- ስማቸው የተጻፈበትን የተለያዩ ቀለማት ከካርታው ጋር ለማገናዘብ ልብ ማለት ይገባል። በዚህ መሠረት ከስዕሉ ላይ በቀላሉ ለመረዳት

## ከሂትሮው ለምንመጣ

ፒካዲሊ መስመር ምስራቅ አቅጣጫው (Picadilly line east bound) ወደ ኮክፎስተርስ የሚሄደውን ባቡር በመያዝ ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ በዚያው ባቡር እንደርሳለን ።

## ከቪክቶሪያ ለምንመጣ

በመጀመሪያ ቪክቶሪያ መስመር ሰሜናዊ አቅጣጫ (Victoria line North bound ) ወደ ዋልታምስቶው ሴንትራል(Walthamstow Central) የሚሄደውን ባቡር በመያዝ ከዚህ ቀጥሎ ያለው መቆሚያ ወይም ግሪን ፓርክ ባቡር ጣቢያ

ሲቆም እንወርድና እዚያው ጣቢያ ፒካዲሊ መስመር ምስራቅ አቅጣጫ (Picadilly line east bound) ወደ ኮክፎስተርስ (Cockfosters) የሚሄደውን ባቡር በመያዝ ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ (Holloway Road train Station) በዚያው ባቡር እንደርሳለን ።

**<u>ከሊቨርፑል መንገድ ለምንመጣ</u>**

አመርስሚዝ እና ሲቲ፣ ሜትሮፖሊታን ወይም ሰርክል የተባሉ አማራጭ የባቡሮች መስመሮች ስላሉ ከነዚህ አንዱን ምዕራብ አቅጣጫቸውን በመያዝ ጉዞአችንን መጀመር እችላለን። ሀመርስሚዝ እና ሲቲ መስመር ከያዝን (Hammersmith and City line west bound) ወደ አመርስሚዝ ፤ ሜትሮፖሊታን መስመር ከያዝን ወደ አመርሻም ፣ዋትፈርድ ወይም ቸሻም ፤ ሰርክል መስመር ከያዝን ወደ አመርስሚዝ ወይም ኤጅዌር ሮድ የሚሄደውን ባቡር አራተኛውና ኪንግስ ክሮስ የሚባለው ባቡር ጣቢያ ላይ ወርደን እዚያ ባቡር ጣቢያ ውስጥ ፒካዲሊ መስመር ምስራቅ አቅጣጫ (Picadilly line east bound) ወደ ኮክፎስተርስ የሚሄደውን ባቡር በመያዝ ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ በዚያው ባቡር እንደርሳለን ።

**<u>ከሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ በዋላስ?</u>**

Fig.4. የሆሎዌይ አካባቢ የመንገድ ካርታ ( Holloway Area Street Map ) ኦዲዎን ሲኒማ




ደብረ ገነት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሚገኝበት ቦታ (+ Crayford Road ) ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ

ከታች ካርታው እንደሚያሳየው ደብረ ገነት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሚገኝበት ቦታ ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ እንዲሁም አቅጣጫቸውና ምልክት ዋና ምልክት ሊሆን ይችላል ማለት የታወቀ ሲኒማን ጨምሮ ላማሳየት ተሞክሯል።

ሆሎዌይ መንገድ ባቡር ጣቢያ እንደ ደረሱ ምናልባት ተቀባይ በተለያዩ ምክያቶች በሰዓቱ ባይገኝ ወይም ባይኖር ከባቡር ጣቢያው እንደወጡ በአውቶብስ በግምት 7 ደቂቃ በእግር 15 ደቂቃ ቢወስድ ነው። አውቶብስ መያዝ ከፈለጉ ከዚያው ከባቡር ጣቢያው መውጫ ላይ 43 ወይም 271 ቁጥር አውቶብስ በመያዝ አራተኛው መቆሚያ ወይም ኦዲዎን ሲኒማ ቤት አቅራቢያ መውረድ አለብዎት።



Fig.5, ደብረ ገነት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ ሲደርሱ የሚያገኙት ቤተ ክርስቲያን ( The Rock Tower)

ከዚያ እንደ ወረዱ በካርታው መሠረት የቀይ ቀስቱን አቅጣጫ ተከትሎ ሲኒማ ቤቱን ካገኙ በዋላ በዚያው መንገድ (Tufnell park Road) ገባ ብለው ትንሽ ወደ እንደተጓዙ ከላይ ያለውን ቤተ ክርስተያን ያገኛሉ። ይህ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ሰዓት ከዚህ በበለጠ ታድሶ ያገኙታል። ከመጡበት አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያኑን ፊት ለፊት እያዩ ወደ CLARETON Road በስተግራ ታጥፈው ወደ ፊት በመጓዝ ከሁለት ደቂቃ ባለወበለጠ ጊዜ ቤተ እኛ ቤተ ክርስቲያን በመድረስ ተመስገን ይላሉ።

## ለንደን ደብረ ገነት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን

Fig.4 አሁን የምንገለገልበት ቤተ ክርስቲያን



የፊት ለፊት ገጽታው



ከአንድ ጎኑ ሲታይ

ጠቃሚ ማስታወሻዎች

- አየር ማረፊያዎች ፡- ሂትሮው ፣ ጋትዊክ፣ስታንስተድ፣ሉተን
- ባቡር ጣቢያዎች ፡- ሂትሮው፣ቪክቶሪያ፣ሊቨርፑል መንገድ፣ሆሎዌይ መንገድ
- አውቶብስ ጣቢያ፡- ቪክቶሪያ ኮች ጣቢያ
- የባቡር መስመሮች፡- ቪክቶሪያ፣ፒካዲሊ፣ ሰርክል፣ሀመርስመዝ እና ሲቲ፣ሜትሮፖሊታን
- ምልክቶች፡- የምድር ውስጥ ባቡር
- ኮች/አውቶብስ፡-

አስፈላጊ ስልክ ቁጥሮች፡- _ መልአከ ገነት ከፍያለው አስቻለው - 07828622095

መልአከ ሰላም አዲስ አበበ - 07958085960

አይናለም መብራቱ - 07949770818

ሀብታሙ አያሌው - 07947900238

ብርሃኔ አፈወርቅ - 07939578460

ቴዎድሮስ ወዳጆ - 07828850919

ሀይሉ አብርሃም - 07727191172

## መልካም መንገድ ይሁንልዎ!